# ግልጽ ደብዳቤ

ለክቡር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል
ቅንጅት ለአንድንትና ዴሞክራሲ
ሊ ቀ መ ን በር
በአሉበት አድራሻ

# ወንድም ኢንጂነር ሀይሉ

ጤና ይስጥልኝ እንደምን ከረሙ ጤንነትዎስ እንዴት ነው፣በአገራችን ነጻነቱን ና ሰብአዊ መብቱን ተግፎ ይሰቃይ የነበረው ሰማኒያ ሚሊዮን ህዝብ መግቢያና መውጪያ አጥቶ ሲንከራተት፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይስማሙ ስለ ተስማሙ በህብረትና በአንድነት ለምስራት ባለመቻላቸው መሳቂያና መሳለቂያ ሆነው ስለቀሩ፣ አርስዎና የትግል ጓደኞችዎ ህዝቡን አሰባስባችሁ በአንድነት ስለአሰለፋችሁት በስድስት ወራት ጊዜ ተደራጅቶ ከመወያየት አልፎ በታሪኩ ታይቶ የማይታወቅ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ስሜቱንና ፍላጎቱን ለመግልጽ በመቻሉ በጣም ደስ ብሎታል።

በጥባጭ ካለ ማን ንጹህ ይጠጣል እንደሚባለው ምሳሌ፣ መለስ ዜናዊ የሚባል የባእድ ቅጥረኛ በሰላም የተከናወነውን ምርጫ በጥብጦ ስለአደፈ
ረሰው፣ አጭበርብሮ ሽፍጦ ዋሽቶ አሽነፍኩ ስላለ የተደረገው ጥረት ሁሉ ድካም ሆኖ ቀረ፤፡ አናንተም ይህንን የተንኮል ስራ በዝምታ ለምቀበል ባለመቻላችሁ ትግላችሁን አስከመጨረሻው ቀጥላችሁ አስር ቤት መግባት ተገደዳችሁ፣ አስር ቤት አንድትገቡ የመከራችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ ቢሆንም አስከ ተፈታችሁበት ቀን ድረስ ክናንት አልተልየም፣በመጨረሻም በውጭ አገር የሚኖሩትን ወገኖቻችሁን ለመነብኘት ወደ አሜሪካ ስትመጡ በመካካካችሁ አለመግባባት ተፈጠረ፤ የተበደለ ተክሶ፣ያጠፋ ተወቅሶ አርቅ እ ንዲደረግ ቢሞከርም ስአልተቻለ፣በዚህ የእርስ በእርስ ሹኩታ የተጠቀመው መለስ ዜናዊ ብቻ ነው፣ የእናንተ ከአገር መውጣት ለመለስ ታላቅ አረፍት ስለሰጠው ሀይሉን አጠናከረ፣ የእሱን ወገኖች በይፋ ሾመ ሸለመ በጎንደር ያለውን ግዛት ለሱዳን ሸጠ፣ በዚያ አእካባቢ የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያን አስሮ ውደ ኢትዮጵያ ላከ።

ይህንን ግልጽ፤ ደብዳቤ ለመጻፍ የተገደድኩት ኢንጂነር ሀይሉ ሻውልን በፋክስ በስልክ በ ኢሜይል ለማግኘት ሞክሬ ስላአቃተኝ በአኢንተርኔት ሙክራ ለማድረግ ነው።

ውንድም ኢንጂነር ሀይሉ፣ አርስዎና የትግል ጓድኞችዎ ለብዙ ምእት አምታት ተኝቶ የነበረውን የኢትዮጵያ ህዝብ ከአንቅልፉ ቀስቅሳችሁ በ 1997 በተደረገው ስላማዊ ስልፍ አይዞህ ተነሳ ብላችሁ አደባባይ ላይ እንዲፎክር እንዲሸልል የሞተ ወኔውን በመቀስቀስ የድሉን መንገድ ካሳያች
ሁት በኋላ ለምን ድምጻችሁ ጠፋ? ሞታችንም ሽረታችህንም ከህዝብ ጋር ነው ከአናንት ብንለይ ኢትዮጵያ ትለይን ብላችሁ ለህዝቡ የሰጣችሁትን ቃል ረሳችሁ? አይመስለኝም፤

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ካለበት ኑሮ፣ ከመለስ ዜናዊ ቀንበር ለማላቀቅ ለኢትዮጵያ ህዝብ የምንሞተው አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከተቻለ ደጋግመን አንሙትልት;፡ ሞፈርና ቀንበር ተሸክሞ በከፈለው የግብር ገንዘብ ያስተማረን አባት፣ በጅርባዋ የማገዶ እንጨት በክንዶቿ አኛን አዝላ ያሳደገች አናት ብንሞትላቸው ሞት በዛብን?

ከአስር ቤት ተለቃችሁ በወጣችሁበት ጊዜ በመላ ኢትዮጵያ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አስረኞች እንደነበሩ ታስታሳላችሁ? አነዚህ እስረኞች አንፈታለን ብለው የሚጠብቁት እናንተን ነው፣ ለምን ረሳችኋቸው፣ ተስፋ ቆርጠው ራሳቸውን አደጋ ላይ ቢጥሉ አይጸጽታችሁም? የርስዎ ድምጽ መጥፋት ለሁላችንም ኣንቆቅልሽ ሆኖብናል; በድምጽዎ መጥፋት ብዙዎች ተስፋ በመቁረጥ ወደ ጠላት ጎራ ገብተዋል፤ ግማሹም ደካማ ስልሆነ ወያኔ ገዝቶት ሰላይ መሆን ተገዷል።ድምጽዎ የጠፋው በጤንነት ምክንያት ክሆነ ይህንን በመግለጫ መልክ በየጊዜው ቢያወጡ ህዝቡ ከስጋት ይድናል ወይም በቅርቡ ወደ አእገራቸው ሊመለሱ ነው ክተባለ በኋላ ድምጽዎ ሲጠፋ በጎን ደግሞ ብዙ ነገር ይወራል;

በአሁኑ ውቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ያለመሪ ያለ ሰብሳቢ ስልቀረ መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ኢትዮጵያን በሙሉ ሰይሸጧት ወይም ከአለም ካርታ ሰይፍቋት እንድረስላት.። ኢትዮጵያ ብዙ ልጆች ወልዳ የወላድ መካን ስለሆነች ምሁራን የሚባሉት አዋቂዎቿ ተጸይፈዋት ሲሸሹ አንድ ቀን የድል አጥቢያ አርበኞች ህነው መምጣታቸው አይቀርም፡ የቀሩትም መለስ ዜናዊ ክንድ ላይ ተንጠልጥለው ጥዋትና ማታ ያእርፍት እዬጠቧት ነው፣ ኢትዮጵያ ጉያ ተሰብስበወ የሚጠብቋት የበኩር ልጆቿ ገበረዎች ብቻ ናቸው። ኢንጂነር ሀይሉ፡ የጀመሩት ስራ በጣም አድካሚ ቢሆንም መላው የአትዮጵያ ህዝብና የኢትዮጵያ አምላክ ከርስዎ ጋር ስለሆነ መጨረሻ ውን ለማየት እድሜ ይስጠን።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ጌታቸው ጋረደው

ሚያዚያ 24/2000 02.05.2008